ሕያው ተስፋ ድምጽ
በየሶስት ወሩ እየታተመ የሚወጣ
አዘጋጅ፡- የሕያው ተስፋ ስነጽሁፍ ክፍል
ግንቦት 2002

# ታውቃላችሁን

## ርዕሰ አንቀጽ

ለክቡራን አድማጮቻችን፤ የአገልግሎት አጋሮቻችንና አንባቢያን በሙሉ ሠላምታችንን በክርስቶስ እየሱስ ወደእናንተ እናቀርባለን፡፡ ባለፈው ሁለተኛው ዙር እትማችን በተለያዩ ርዕሶች መልእክት ማስተላለፋችን ይታወሳል፡፡ በዚህ በሶስተኛ ዙር ጋዜጣችን በአብዛኛው ያተኮርነው የክርስቲያንን ዝግጅትን በተመለከተ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሁላችንንም የሚመለከትና በየእለቱ ሊያሳስበን የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ስለሆነም የዘመኑን ፍጻሜ ምን ላይ እንደደረሰ ለመረዳት ስለ ዓለም የተተነበዩት የትንቢት መልእክቶች ምን ደረጃ ላይ ደርሰዋል? ስለቤተክርስቲያንና ስለ እስራኤልስ ምne የተነገረና የተፈጸመ መልእክት አለ? ለሚሉት ጥያቄዎች ይህች አነስተኛ ጋዜጣ ማብራሪያን ትሰጣለች፡፡

እንዲሁም ከዚህ በተጓዳኝ በጥያቄዎ መልስ አምዷ የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስ መምጣት ቀን ቆርጠውና ቀምረው በዚህ ቀን ይመጣል!! የሚሉ አሉና ምን ትላላችሁ? ለሚለው ጥያቄ ሰፊ ትምህርት አዘል ማብራሪያን አቅርባለች፡፡

በተጨማሪም ለምጻቱ ዝግጅት የሚጠቅሙ ልዩ ልዩ ትምህርቶችን እንደ የቤተክርስቲያን ተሳትፎ አስፈላጊነት ፤ የክርስቲያን ህብረት ጥቅም፤ እንዲሁም በእግዚአብሄር እይታ ስንታይ እንዴት መስተካከል እንዳለብን የመሳሰሉትን በማካተት ከአንዳንድ እውቀ ሰዎች የህይወት ምስክርነት ጋር ተቀናጅታ ቀርባለች፡፡

ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም በክብር መገለጫው ወቅት ስለሚኖረው ሁኔታ ከተናገራቸው ሃሳቦች ሁለቱ ለክርስቲያን ጥንቃቄ የሚጠቅሙ ናቸው አነዚህም አንደኛው፡- “ ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ እምነትን ያገኝ ይሆንን?” የሚል ሲሆን ሁለተኛው፡- “ነገር ግን ብዙዎች ፊተኞች ኋለኞች ኋለኞች ፊተኞች ይሆናሉ!!“ የሚሉ ናቸው ፡፡ ወደ እየሱስ ከመጣንበትና ዳግመኛ ከተወለድንበት ጊዜ አንስቶ አሁን እስካለንበት ሰዓት ድረስ በብዙ ፈተናዎችና ውጣ ውረዶች አልፈን፤ ስለክርስቶስ ወንጌል ዋጋ ከፍለን ፤ብዙ አገልግለን፤ መስክረንና ሰብከን፤ በመንፈሳዊ ሕይወት ፊተኞች ሆነን፤ በዚህ እምነትና ፍቅር በጎደለበት መጨረሻ ዘመን ኋለኞች ብንሆን እንዴት ያሳዝናል!!

ስለዚህ ዓለም በፈለገው ጥበብና እውቀት ብትመጥቅ ፤ ሐጢአቷ እስከሰማይ ቢደርስ፤ ሰዎች ለገንዘብ ለሐብትና ለክብር ቢሯሯጡ፡ እኛ ግን ከክርስቶስ ጋር ከቃሉና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተጣብቀን በልባችን የላይኛውን መንገድ እያሰብን ልንጓዝ ይገባል፡፡ ለዚህም ከሚረዱን ነገሮች አንዱና ዋነኛው የትጋት ጸሎት ነው!! እየሱስ እንዲህ አለ “ እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማምለጥ በሰውልጅም ፊት ለመቆም አንድትችሉ ስትጸልዩ ሁልጊዜ ትጉ!! ሉቃስ ም.21 ቁ 36 ፡፡

ከአዘጋጁ!!

## የ ሚካኤል ፋራዳይ ክርስቲያናዊ ሕይወት

በመጠቀው የሳይንስ ምርምሩ ታሪክ ዘመን ሚካኤል ፋራዳይ የሕዝብ አድናቆት የተቸረው እንደ ኮከብ ለአያሌ ዓመታት ያበራ ሰው ነው፡፡ ስለዚህ ደማቅ ሳይንሳዊ ስራው ብዙ ጸሐፍትና የሳይንስ ተመራማሪዎች ጥናት አድርገውበታል ብዙ ዘክረውለታል ፡፡ ከዚህ ያለፈ ያልተመረመረና እንደ ድንግል መሬት ያልታረሰ ያልተጻፈለት የሚካኤል ፋራዳይ ሌላ የግል ህይወትና አኗኗር እምነት ገርበብ ያለውን የጓዳውን በር ገለጥ አድርገው በመጠኑም ቢሆን የሚያስቃኙን እንደ ታይዶል ቀጥሎ ግላድስቶን እና ሌሎች በርሱ ዘመን የነበሩ ጸሐፍት ስለ እውቁ ሳይንቲስት ፊር ቀዳጅ ብርሃን የፈነጠቁልን ናቸው ፡፡

በሳይንሱ ዓለም አንቱታን የተቸረው ይህ ሊቅ የግልና የጓዳ ሕይወቱ ሲገለጥ የሰንዴማንያ ቤተ ክርስቲያን አባልና ሽማግሌ መሆኑን አልፎ አልፎ በየሰንበቱ የምክር ቃል ወይም ስብከት አገልግሎት በማድረግ ቤተክርስቲያኑን ያገለግል የነበረ ትጉህ ክርስቲያን እንደነበረ ድርሳን የፈተሹ መስክረውልናል፡፡ ዛሬ የምናስተዋውቃችሁ ሳይንቲስቱን ሚካኤል ፋራዳይን ሳይሆን ክርስቲያኑን ሚካኤል ፋራዳይን ነው፡፡

ሳይንቲስትነትንና ክርስቲያንነትን ሁለት የሚቃረኑ የሚመስል ሕይወትን አንድ አድርጎ አጣምሮ ስለኖረው ሚካኤል ፋራዳይ አያሌ ጥናቶች በጠበብት የተደረገ ቢሆንም ስለክርስትና ሕይወት ልምምዱ የተጻፈው እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ማን ይመስክር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ እንደተባለው በዘመኑ በነበሩት ጸሐፍት ከቀረቡት ጽሁፍና እንዲሁም በቤተክርስቲያን ተመዝግበው ከሚገኙት ስብከቶቹ በምን አይነት ደረጃ ክርስትናን ይኖረው እንደነበረ ማወቅ ተችሏል፡፡

በዘመናት ሁሉ ከተደረጉ ጥናታዊ ምርምሮች በዓለማችን ታሪክ ውስጥ ሥራቸው እንደ ኮከብ ከሚያበራ የዓለማችን ባለውለተኛ ሳይንቲስቶች ከዋነኞቹ የሚመደብ መሆኑን በሁሉም ዘንድ የታመነ ነው፡፡ እንዳንድ የሳይንስ ምርምሩ ዘመን ታሪክ ተመራማሪዎች የፋራዳይን ምርምርና ሥራውን እጅግ ከማድነቃቸው የተነሳ የሳይንስ ምርምሩ ታሪክ ዘመን “አቻ ያልተገኘለት ምርምር አድራጊ” በማለት በሕያው ታሪኩ ላይ ነስንሰውበታል፡፡

ሚካኤል ፋራዳይ በሳንዴማንያ ቤተክርስቲያን አባል ከሆኑ ወላጆቹ ተወልዶ በሳንዴማንያ ቤተክርስቲያን ክርስትናን ተቀብሎ የተለማመደና ያደገ እንደ ብርሃን የሚታይ ራሱን ለጌታ ያስገዛ አማኝና እስከ እለተ ሞቱ ድረስ የቤተክርስቲያኒቱ አባል የነበረ ነው፡፡ በተጨማሪ ከ1840 —1844 እንዲሁም 1860-64 ድረስ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ሆኖ በመሪነት አገልግሏል፡፡

ታይዶል ስለሚካኤል ፋራዳይ ባህርይ በጻፈው አውደ እለት ላይ ፋራዳይ የእርሱን እምነት ሰዎች እንዲቀበሉ የማስገደድ ባህርይ ያለው ሰው አልነበረም፡፡ ይህንንም ልምድ የቀሰመው ከቤተክርስቲያኒቱ ባህል እንደሆነ ይገመታል፡፡ ምክንያቱም የቤተክርስቲያኒቱ አባላት እርስበርሳቸው አጥብቀው የሚዋደዱ ፍቅር ያላቸው

ቢሆንም ወንጌል ለሌሎች በማድረሱ ስራ ብዙ የታወቁ አልነበሩም ስለዚህም በአስራአምስት አመታት የጠበቀ ወዳጅነታችን ዘመን እራሴ ስለእምነትና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች አንሰቼ እስከተናገርኩበት ቀን ድረስ ፋራዳይ አንድም ቀን ተናግሮኝ አያቅም ፡፡

በገዛ ፈቃዴ የልቤን በር ከከፈትኩለት ጀምሮ ግን ሳይፈራና ሳያወላውል፡ በግልጽነትና በድፍረት ሃይማኖታዊ በሆነ ርዕሶች ላይ አናግሮኛል ብሏል፡፡

ታይንዶል የፋራደይ የሥራ ባልደረባ ሲሆን ከፋራዳይ በመቀጠል የሮያል ኢንስቲቱዩሽን መሪ በመሆን ተክቶ የሠራ ሰው ነው፡፡ አውደ እለት አመዘጋገቡ የሳይንቲስታዊ ሥራዎቹ ላይ ያተኮረ ቢሆንም ስለግል ባህርዮቹ የከበረና ጨዋነትን የተላበሰ ነበር ብሎታል፡፡ ከዚያም አልፎ፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ኤጲስ ቆጶሳት አመራረጥ ለጢሞቴዎስ በጻፋቸው መስፈርቶች ላይ የተዘረዘሩትን የማይነቀፍ፤ ልከኛ ፤ ራሱን የሚገዛ፤ እንደሚገባ የሚሠራ ፤ ለማስተማር የሚበቃ የሚሉትን ባህርያት ሙሉ በሙሉ በፋራዳይ